የመ/ቁ. 16270

ታህሣሥ 17 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
አቶ ሐጐስ ወልዱ
አቶ ዳኜ መላኩ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች ...አዋሳ እርሻ ልማት ድርጅት ነገረፈጅ አቶ ጀማል አህመድ ቀረበ

ተጠሪ..... አቶ መሐሪ ማታ ጠበቃ አቶ ተሰማ አበበ ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለሰበር ለቀረበው አቤቱታ መነሻ የሆነው ተከሣሽ የሆነው የአሁኑ አመልካች መኪናው አድርሷል በተባለው የግጭት አደጋ ምክንያት ለተጐጂው ለአሁኑ ተጠሪ የጉዳት ካሣ ብር 28,800፣ የሞራል ካሣ ብር 1000 እና የህክምና ወጪ ብር 308 በጠቅላላው ብር 30,198 እንዲከፍለው መወሰኑ ነው፡፡

ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ ከሣሽ የሆነው የአሁኑ ተጠሪ ሐምሌ 15 ቀን 1987 ዓ.ም በሞተር ሣይክል በመንገዝ ላይ እያለ ንብረትነቱ የአዋሳ እርሻ ልማት ድርጅት በሆነ የሰሌዳ ቁጥር 3-00217 መኪና ተገጭቶ አንድ እግሩ በመጐዳቱ ወይም በመቆረጡ ምክንያት ከአደጋው በፊት እየሰራ ያገኝ የነበረው ገቢ መቋረጡን በመግለጽ የመኪናው ባለቤት በሕግ ባለበት ኃላፊነት መሠረት የጉዳት ካሣ ብር 58,600 እንዲከፍለው የሚጠይቅ ክስ ለሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱ በኃላፊነቱ ጉዳይም ሆነ በካሣው መጠን ላይ ካከራከረና ማሥረጃም ከሰማ በኋላ ጉዳቱን ያደረሰው የተከሣሹ የአዋሳ እርሻ ልማት ድርጅት መኪና መሆኑ ስለተረጋገጠ ለደረሰው ጉዳት በሕግ ኃላፊነት አለበት፣ ተጐጂው በተከሣሹ መኪና ባይገጭ ኖሮ እግሩ ሊቆረጥ አይችልም ነበር፣ እግሩ ከተቆረጠ ደግሞ ቀደም ሲል ሲሰራ የነበረውን ሥራ ተመልሶ ለመሥራት እንደማይችል ግልጽ ነው፡፡ በአካሉ ላይ የደረሰው ጉዳትም 50% እንደሆነ ስለተገለፀ ይህንኑ ግምት ውስጥ በማስገባት በክሱ የጠየቀውን



የጉዳት ካሣ በከፊል በመቀነስ ለደረሰበት ጉዳት ብር 28,800 የሞራል ካሣ ብር 1000 እና ለህክምና ያወጣውን ወጪ ብር 308 በጠቅላላው ብር 30,198 ሊከፍለው ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልካች የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በኃላፊነቱ ጉዳይም ሆነ የካሣውን መጠን በማስመልከት የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ.3144 የይግባኝ አቤቱታ ሊያቀርብ የቻለ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የአሁኑ ተጠሪ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥበት አድርጐ የይግባኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በመጨረሻ ግንቦት 19 ቀን 1996 ዓ.ም መርምሮ በሰጠው ውሣኔ ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሣኔ የሚታይበት ጉድለት የለም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ. 348(1) መሠረት አጽንቶታል፡፡

አመልካች የክልሉ ሁለት ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ በተመሣሣይ መንገድ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በሚል ምክንያት በዚህ መዝገብ ለሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመወሰኑ አመልካች በ30/10/96 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው ማመልከቻ ለአሁኑ ተጠሪ ተልኮ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ በጠበቃው አማካኝነት ጥቅምት 5 ቀን 1997 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በበኩሉ በተጠሪው ጠበቃ በኩል በጽሑፍ የተሰጠውን መልስ ከተመለከተ በኋላ የመልስ መልስ ጽፎ ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ አድርጓል፡፡

ችሎቱም የኃላፊነቱን ጉዳይም ሆነ የካሣውን መጠን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በቅድሚያ የአሁኑ አመልካች በተጠሪው ላይ ለደረሰው ጉዳት በሕግ ኃላፊነት አለበት የለበትም? ጉዳቱ የደረሰው በተጐጂው(ተበዳዩ) በገዛ ራሱ ጥፋት ነው ለማለት የሚያስችል ምክንያት አለ ወይንስ የለም የሚለው ሲመረመር በፍሬ ነገር ረገድ የአሁኑ ተጠሪ ሞተር ሣይክል እየነዳ በመንገዝ ላይ እያለ ሁለተኛው ተከሣሽ ሲያሽከረክረው በነበረው ንብረትነቱ የአሁኑ አመልካች በሆነው የሰሌዳ ቁጥር 3.00217 መኪና ገጭቶ ከነሞተር ሣይክሉ በመውደቁ ምክንያት በአንድ እግሩ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበት የተቆረጠ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ካሣ የተጠየቀበት ጉዳት መነሻው የአሁኑ አመልካች መኪና ያደረሰው የግጭት አደጋ ሆኖ ከተገኘ ጉዳዩ ከውል ውጭ ስለሚደርስ ኃላፊነት የሚመለከት ነው፡፡

የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2081(1) የአንድ መኪና ወይም የአንድ ባለሞተር ተሽከርካሪ ባለቤት የሆነ ሰው አደጋውን ያደረሰው መኪናውን ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪውን ለመንዳት ወይም ለማንቀሣቀስ ባልተፈቀደለት ሰው ቢሆንም እንኳን መኪናው ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪው ላደረሰው ጉዳት አላፊ የሚሆነው ባለሀብቱ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ የአንድ መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ባለቤት አጥፊ ሣይሆን ጉዳት ያደረሰው መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ባለሀብት በመሆኑ ብቻ ለደረሰው ጉዳት በሕግ አላፊ ይሆናል፡፡ ተጉጂው ወይም ተበዳዩ ጉዳቱ የደረሰው በተከሣሹ መኪና መሆኑን ከማሥረዳት ውጭ በባለሀብቱ በኩል ጥፋት ስለመኖሩ ማረጋገጥ አይጠበቅበትም፡፡

በሌላም በኩል ጉዳት ያደረሰው መኪና ባለሀብት ከአላፊነት የሚድንባቸው የሕግ ምክንያቶች ያሉ ሲሆን ከእነዚህም አንዱ ጉዳቱ የደረሰው በተጉጂው ወይም በተበዳዩ ጥፋት ምክንያት እንደሆነ አላፊነት አያመጣም በሚል በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2066(2) ላይ የተመለከተው ነው፡፡ ጉዳት ያደረሰው መኪና ባለሃብት ጉዳቱ የደረሰው በተጉጂው ጥፋት ምክንያት ነው የሚል መከላከያ ካለው የማስረዳት ሸክም የራሱ ይሆናል፡፡ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2086(2) ላይ እንደተመለከተው የአንድ መኪና ባለሀብት ጉዳቱ የደረሰው በከፊል ወይም በሙሉ ከተበዳዩ ጥፋት የተነሣ መሆኑን ካላረጋገጠ በቀር በከፊልም ሆነ በሙሉ ከአላፊነቱ ሊድን አይችልም፡፡

በቀረበው ጉዳይ የአሁኑ አመልካች ለደረሰው ጉዳት በተበዳዩ በኩል ጥፋት አለ በማለት የሚከራከረው በሁለት ምክንያቶች ሲሆን አንደኛው ተጠሪው የሌላ ድርጅት ሞተር ሣይክል ሰርቆ እየነዳ ሲሄድ ነው የተገጨው በሚል የቀረበ ነው፡፡ የተሰረቀን ሞተር ሣይክል ወይም ሌላ ባለሞተር ተሽከርካሪ በሚነዳ ሰው ላይ ጉዳት ማድረስ በአላፊነት አያስጠይቅም የሚል ሕግ የለም፡፡ የጉዳቱም መንስኤ ተበዳዩ የተሰረቀ ሞተር ሣይክል ይዞ መገኘቱ ወይም መንዳቱ ሣይሆን የአመልካችን መኪና ሲያሽከረክር የነበረው ሾፌር መንገዱን በማጥበብ ተጠሪው የሚነዳውን ሞተር ሣይክል ሊገጨው መቻሉ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ተጠሪው የተሰረቀ ሞተር ሣይክል እየነዳ ሲጓዝ ነው የተገጨው በሚል ያቀረበው ክርክር ሕጋዊ መከላከያ ሊሆን አይችልም፡፡ ሁለተኛው ሞተር ሣይክል ለመንዳት የሚያስችል መንጃ ፈቃድ የለውም የሚለው ነው፡፡ መንጃ ፈቃድ የሌለው መሆኑ ብቻ ጉዳቱ የደረሰው በእርሱ ጥፋት ነው ለማለት አያስችልም፡፡ መታየት የሚገባው ሞተር ሣይክሉን እየነዳ ሲጓዝ የፈፀመው ጥፋት ምንድነው የሚለው ነው፡፡



የአሁኑ አመልካች ደግሞ ተጠሪው መንጃ ፈቃድ የሌለው መሆኑን ከሚገልጽ በቀር በሥር ክርክሩ ወቅት ተጠሪው የፈፀመው ጥፋት መኖሩን አላስረዳም፡፡ መንጃ ፈቃድ ሣይኖረው የሚያሽከረክርን ሰው በመኪና መግጨት በሕግ በአላፊነት ከመጠየቅ ሊያድን ስለማይችል አመልካች በዚህም ረገድ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ በአጠቃላይ የአሁኑ አመልካች መኪናው ላደረሰው ጉዳት አላፊ ነው ተብሎ በመወሰኑ የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም፡፡

የካሣውን መጠን በተመለከተም ተጉጂው የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች መኪና በተፈፀመው ግጭት የተነሣ አንድ እግሩ የተቆረጠ መሆኑ የተገለፀ ሲሆን በእግሩ መቆረጥ ምክንያት ቀደም ሲል የተሰማራበትን ሥራ ለመቀጠል አልቻለም፡፡ ከአደጋው በፊት በወር ብር 120 ደመወዝ እየተከፈለው ሲሰራ የነበረ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማሥረጃ ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ላየው ለሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት መቅረቡን ከተሰጠው ውሣኔ ለመረዳት ተችሏል፡፡ የአሁኑ አመልካች ይህንን የሚያፈርስ ሌላ ተቃራኒ ማሥረጃ አላቀረበም፡፡ ፍ/ቤቱም በተጠሪው በደረሰበት አደጋ ምክንያት ገቢው ሊቋረጥ መቻሉንና ጉዳቱም ዘለቄታ ያለው መሆኑን በመገንዘብና ከአደጋው በፊት በየወሩ ሲያገኝ ነበር የተባለውን ደመወዝ በመነሻነት በመጠቀም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2102(1) መሠረት የጉዳት ካሣውን ልክ በርትዕ በማመዛዘን ወስኗል፡፡ የካሣ አከፋፈልና ልክ የሚወሰነው ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2090 ጀምሮ በተከታታይ በተፃፉ ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡ የመጀመሪያው ቁጥር 2090(1) በመደቡ በጉዳቱ ምክንያት ተበዳዩ የሚካሠው ለጉዳቱ ተመዛዛኝ የሆነ ኪሣራ በመክፈል እንደሆነ የሚገልጽ ሲሆን ቁጥር 2091 ደግሞ ለደረሰው ጉዳት አላፊ መሆኑ በሕግ የታወቀው ሰው የሚከፍለው የጉዳት ካሣ አላፊነቱን ያመጣው ጉዳይ በተበዳዩ ላይ ከደረሰው ጉዳት ጋራ እኩል ሆኖ መመዛዘን እንዳለበት የሚደነግግ ነው፡፡ ቀጥሎ ያለው ቁጥር 2092 ሲታይ ለወደፊት ሊደርስ ይችላል ተብሎ የሚገመተው ጉዳት የተረጋገጠ በሆነ ጊዜ እስኪፈፀም ድረስ ሣይጠበቅ ካሣ ሊከፈል የሚገባ መሆኑን ያስረዳል፡፡ ከዚህ ሌላ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2102(1) ላይ የሠፈረውን ድንጋጌም ስንመለከት ስለጉዳቱ ምን ያህል ኪሣራ እንደሚከፈል በትክክል ለመወሰን ያልተቻለ እንደሆነ ዳኞች የነገሮቹን ተራ ሁኔታዎችንና ተጉጂውም ያደረገውን ጥንቃቄ አመዛዝነው በመገመት የኪሣራውን ልክ በርትዕ እንዲወስኑ የሚፈቅድ ነው፡፡

በዚህ መዝገብ በቀረበው ጉዳይ የጉዳት ካሣው መጠን ስለመብዛት አለመብዛቱ ከላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች አንፃር ሲመረመር በተጉጂው በአሁኑ ተጠሪ ላይ በመኪና

ግጭት በደረሰው አደጋ ምክንያት አንድ እግሩ ሊቆረጥ መቻሉ ከአደጋው በፊት እየሰራ ሲያገኝ የነበረውን ገቢ ያስቀረበት መሆኑ ብቻ ሣይሆን ወደፊት የሚኖረውን የኢኮኖሚ እድገት እንደሚጐዳው ይገመታል፡፡ በነበረው ሥራ በመቀጠል ወይም በሌላ ሙያ በመሰማራት የራሱን የገቢ ምንጭ ሊያሻሽልና ሊያሣድግ ይችላል፡፡ በደረሰበት አደጋ የአንድ እግሩ መቆረጥ ደግሞ በዚህ የወደፊት እድሉ ላይ ሁሉ ተጽእኖ ያደርጋል፡፡

ይህ ሁሉ ሲታይ በወቅቱ የ23 ዓመት እድሜ ነበረው የተባለው የአሁኑ ተጠሪ በዋናው መንቀሣቀሻ በእግሩ ላይ የደረሰው ከፍተኛ ጉዳት እና ይኼው ባለው የኢኮኖሚ ጥቅም ላይ ያስከተለው ጉዳት ተመዛዝኖ በርትዕ ብር 28,800 ካሣ እንዲከፈለው መወሰኑ በሕጉ እይታ በዝቷል ለማለት አይቻልም፡፡ የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ቀርቦለት በነበረው ክሥ መነሻ ጉዳዩን መርምሮ የጉዳት ካሣ ብር 16.000 እንዲከፈለው ከወሰነ በኋላ በይግባኝ ጉዳዩን የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች መከላከያ መልስ እና ማሥረጃ አቅርቦ ክርክርና ማሥረጃው ከተጠናቀቀ በኋላ መወሰን አለበት ብሎ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሠረት ጉዳዩን ከመለሰለት በኋላ ከሣሹ የአሁኑ ተጠሪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.91(1) መሠረት ክሱን አሻሽሎ እንዲቀርብ ተፈቅለት በአዲስ መልክ ክርክሩ ተካሂ በመጨረሻ በሰጠው ውሣኔ የካሣውን መጠን ከፍ አድርጐ በመወሰኑ ተፈጽሟል የምንለው የሕግ ስህተት የለም፡፡ ጉዳዩ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሠረት ለመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተመልሶ ከተላከ ፍ/ቤቱ በመጀመሪያው ውሣኔ ሣይገደብ የካሣውን መጠን ዝቅ ወይም ከፍ አድርጐ ከመወሰን የሚከለክለው ሕግ የለም፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ጉዳይ በኃላፊነቱ ጉዳዩም ሆነ በካሣው መጠን አወሳሰን ረገድ ተፈጽሟል የሚባል የሕግ ስህተት አልተገኘም፡፡

ው ሣ ኔ

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንን ጉዳይ በማስመልከት በይ/መ/ቁ.3144, ግንቦት 19 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ በተደረገው ክርክር ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡



የሰበር መ/ቁ 18581

ህዳር 20 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. አቶ ፍሰሀ ወርቅነህ
3. ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
4. ወ/ሮ ሆሳዕና ነጋሽ
5. አቶ አሰግድ ጋሻው

አመልካች፡- በአ/አ እስላማዊ ድርጅት የአወሊያ ጤና ጣቢያ

ተጠሪ፡- ሲ/ር ቀቡላ ከድር

*የስራ ውል መቋረጥ፣ የካሣ፣ አከፋፈል እና የስንብት ክፍያ አዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 23/1/፣ 43/3/፣ 40/1/2፣44*

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ብተተጠሪ እስከ 6 ወር የሚደርስ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏት ወደ ስራ ትመለስ በማለት ውሳኔ በመስጠቱና የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ በማፅናት ሆኖም የ3 ወር ውዝፍ ደመወዝ ብቻ ይከፈላት ሲል ውሳኔ መስጠቱን ተከትሎ የቀረበ አቤቱታ

ውሳኔ፡- የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ እና ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔ በድምፅ ብልጫ ተሽሯል፡፡

1. በአዋጁ የሥራ መልቀቂያ አለማቅረብ የስራ ውል ማቋረጫ ምክንያት አይደለም፡፡
2. የሠራተኛው የስራ ውል ቀጥሎ ወደ ስራ ቢመለስ በአሰሪው ድርጅት ህልውና ላይ ችግር የሚያስከትል ከሆነ ሠራተኛው ህጋዊው ካሣ ተከፍሎት ከስራ ይሠናበታል፡፡